# የሕዝብ ዝምታ ለፖለቲካ ነጋዴወች ሽፍጥ መደላድል ነው (ከይገርማል) 19.10.2018

*ሀገራዊ ጉዳይን በተመለከተ*

የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ የሚያሳዝን ሕዝብ ነው። ሰላም የመፈለጉን ያህል ሰላም አላገኘም፤ ሀገሩን ወዳድ ቢሆንም የሀገሩ ባለቤት ሊሆን አልቻለም፤ በዕኩልነት ተሳስበን በአንድነት እንኑር ቢልም ከተወሰነ አካባቢ በሚነሱ መጥፎ ሰዎች ከዜግነት ደረጃ ወርዶ በዘር ተከፋፍሎ ተገዥ እንዲሆን ተፈርዶበታል። ለሕዝብ ጥቅም ነው የተደራጀነው፤ አዛዣችንም ሕዝብ ነው እያሉ ሀገር የሚያስለቅሱ ፖለቲከኞች ሕዝቡን ከምንም እንደማይቆጥሩት ዶ/ር ዐቢይ ከተናገሩት መረዳት ይቻላል። በአንድ ወቅት የተደረገውን ሕዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ አስመልክተው ጠ/ሚኒስትሩ ሲናገሩ መንግሥት በሆደሰፊነት በትዕግስት ስላለፈው እንጂ ሁለት ሦስት ጥይት በመተኮስ ተቃውሞውን መበተን ይቻል እንደነበር ነው ያረጋገጡልን። ዕውነቱ ይኸው ነው፤ ሕዝብን መናቅ። ሰዎች ሳይዘጋጁ የሚናገሩት ነገር ቢኖር ከዚያ መሀል ነው ትክክለኛ ስሜታቸውን ማወቅ የሚቻለው። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ሰላማዊ ሰልፍ የሚደረገው ድጋፍን ወይም ተቃውሞን ለመግለጽ ነው። መንግሥት በበኩሉ ወኪሎቹን ልኮ ለድጋፉ ምስጋና ያቀርባል፤ ተቃውሞ ከሆነ ደግሞ የተቃዋሚወችን ቅሬታ ሰምቶ መፍትሄ ወደሚሰጠው አካል ያስተላልፋል። እኛ ሀገር ግን እንዲህ አይነት እድል የለም። የተቃውሞ ሰልፍ ልክ መንግሥትን ለመገልበጥ እንደሚደረግ እንቅስቃሴ ነው የሚታየው። እና የታጠቀ ኃይል በገፍ ይላክና ሰልፈኛውን ማዋከብ ዋና ስራ ይሆናል፤ በዚህ ምክንያት ሰላማዊ ሰልፉ ወደአመጽ ይቀየራል። በጉልበት እየገዙን ያሉት ኃይሎች በትናንሽ ነገሮች ሁሉ የሚዋሹት የውጭ ተመልካቾችን ሰግተው ወንጀላቸውን ለመሸፋፈን እንጂ ሕዝቡን ስለፈሩም ሆነ ስላከበሩ አይደለም ያልሁት ዛሬ አይደለም። ቢያከብሩንና ቢፈሩን ኖሮ መቸ ይኸ ሁሉ ግፍ ይፈጸምብን ነበር! ሕዝቡን የሚፈራና የሚያከብር መንግሥት እንዴት አድርጎ ነው በሰበብ አስባቡ የራሱን ዜጋ በየቀኑ የሚገድል፤ በሞቶ ሺህ የሚቆጠር እስረኛ አድርጎ በወህኒቤት የሚያሰቃይ፤ በሚሊዮን የሚቆጠር የሚያፈናቅል? ከድሀ አፍ እየሞጨቀ ተከፋፍሎ የሚበላ?

ወገኖቼ! ፖለቲካ ለብዙወቹ ትልቅ ቢዝነስ ነው። ወደቢዝነሱ የሚገቡት በሰው ጉልበት፣ ሀብትና ህይወት ነግደው ለማትረፍ ነው። በሕዝብ ጉልበትና ሀብት እንደፈለጉ ለማዘዝ እንዲያስችላቸው በቅድሚያ ያሳምናል የሚሉትን ነገር ሁሉ ያደርጋሉ፤ በዚህ መንገድ ሊሳካላቸው ካልቻለ ወደኃይል እርምጃ ይገቡና ምክንያት እየፈጠሩ ፍዳ ያስቆጥራሉ።

አሁን እየሆነ ያለውን ነገር እስቲ ልብ ብላችሁ ተመልከቱት። "ሀገሪቷ በሽግግር ላይ ነው ያለችው፤ ለውጥ አለ፣ ለውጥ አደናቃፊም አለ፣ ነቅታችሁ ጠብቁ" እያሉ እየሰበኩን ነው። ሽግግሩ ከጀርባችን አልወርድ ብሎ ጤና እየነሳን ባለው በኢሕአዴግ ውስጥ ባሉ የሰዎች መሾምና መሻር ላይ የተወሰነ ነው። በእርግጥ ለውጥ የሚባል ነገር የለም ማለት አይቻልም። ምክንያቱም ለውጥ በማንኛውም ነገር ላይ በየሰከንዶች ልዩነት ሳይቀር የሚታይ ነባራዊ ክስተት ስለሆነ። ይህን ጽሁፍ ለመጻፍ ስጀምር የነበርሁት እኔ፣ ጽሁፉን ከጨረስሁ በኋላ ከሚኖረኝ እኔነት ጋር ፍጹም አንድ ሊሆን አይችልም። ይህን ጽሁፍ ለመጻፍ ሁለት ሰዓት ቢወስድብኝ ጽሁፉን ስጨርስ በሁለት ሰዓት አርጅቻለሁ ማለት ነው፤ ይህ በራሱ ለውጥ ነው። በአካላችን ውስጥ ያለው ውስብስብ ስርአት ሳይታወቀን በየጊዜው ለውጥ ያደርጋል። በውስጣዊም ይሁን በውጫዊ ምክንያቶች ማንኛውም ነገር በማያቋርጥ የለውጥ ፍሰት ውስጥ ይጓዛል። ይህም ማለት የአስተዳደር መሻሻል የተደረገ ባይሆንም እንኳ በተለያዩ ምክንያቶች ለውጥ አይቀሬ ነው ማለት ነው። እኛ የምንፈልገው ይህን አይነት ለውጥ አይደለም፤ የምንፈልገው ሥር ነቀል ለውጥ ነው። አዲስ አደረጃጀት፣ አዲስ ሕገመንግሥት፣ አዲስ አሰራር። በኢሕአዴግ ስር ሆኖ ስር ነቀል ለውጥ እናመጣለን ብሎ ማሰብ ደግሞ ከቀልድ የዘለለ ትርጉም የሚሰጥ አይሆንም።

የሆነው ሆነናስ ማን ነው የለውጥ ኃይል፣ ማንስ ነው የለውጥ አደናቃፊው? አቶ ስብሀት እንደሆኑ ከዚህ በኋላ እንኳን ለውጥ ሊያደናቅፉ ለራሳቸውም ፈቃጅ (አልባሽ አጉራሽ) የሚፈልጉ ናቸው። የሙስና እመቤት የሚባሉት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ተሿሚ ናቸው። የደህንነት ኃላፊ ናቸው የሚባሉት አቶ ጌታቸው አሰፋን በስም እንጅ በመልክ የሚያውቃቸው ስለሌለ ከመሀከላችን ላለመሆናቸው ማረጋገጫ የሚሰጥ የለም። አቶ አባይ ጸሀዬ በስብሰባ ላይ እንደነበሩ አይተናል። ዶ/ር ደብረጽዮን፣ ዶ/ር አርከበ እቁባይ፣ አቶ አስመላሽ ወ/ሥላሴ፣ ጀኔራል ሰዓረ መኮንን፣ - - - ከለውጥ ኃይሉ ጋር ተደምረዋል። ይህም ማለት ሁሉም የሕወሀት አመራሮች የለውጥ ኃይል ናቸው ማለት ነው። ታዲያ ማን ነው ለውጥ አደናቃፊው? ትግራይ መሽገዋል የሚባሉት ለውጥ አደናቃፊወች እነማን ናቸው? አቶ በረከት ስምዖን እና አቶ ታደሰ ካሳ (ታደሰ ጥንቅሹ) የዕውነትም ትግራይ ውስጥ እየኖሩ ከሆነ፣ እነሱ ብቻ ናቸው ለውጥ አደናቃፊ ሊሆኑ የሚችሉት ማለት ነው። ይኸ ደግሞ አያስሄድም። በለውጥ ኃይሉ የሚመራው የትግራይ ክልል፣ የለውጥ አደናቃፊወች ምሽግ ይሆናል ተብሎ ሊታሰብ ስለማይች! ታዲያ እየሆነ ያለው ምንድን ነው ቢባል ኢሕአዴግ የዘረፋትን የሀገር ሀብት ይዘው በሰላም እንዲኖሩ ነባር አባላቱን ከነሀጢያታቸው በክብር ሸኝቶ፣ በለውጥ ኃይል ስም አዲስ በላተኛ በቦታው ተክቷል የሚል ነው።

ይህ ስልት የጠቀመው ከማንም በላይ ወያኔን ነው። በዶ/ር ዐቢይ ይመራል የሚባለው የለውጥ ኃይል "በፍቅር እንደመር፣ በይቅርታ እንሻገር" በሚል መርህ ያለፈውን ሁሉ ረስተን ወደፊት እንድናይ ሲሰብክ ለወያኔ መቆሙ ነበር። መርሁ የሚነግረን ባለፉት የወያኔ የአገዛዝ አመታት የተፈጸሙ ወንጀሎችን ረስተን ሁላችንም በፍቅር እንድንጨባበጥ ነው። ታዲያ ወያኔ ከዚህ በላይ ምን ይፈልጋል! ከበቂው በላይ ዘርፏል፤ የሚጠላውን አሰቃይቶ ገድሏል፣ ሀገሪቱን በፈለገው መንገድ ከፋፍሎ በሕዝብ መሀል በቀላሉ የማይነቀል ጥላቻ ዘርቷል። ይኸ ሁሉ ወንጀሉ ተፍቆለት፣ የያዘውንም እንደያዘ ተደመር ሲባል ከዚህ የበለጠ ምን ይፈልጋል? እንዲህ ያለ ዕድል የራስ ካልሆነ ሰው/ቡድን ይገኛል ብሎ ማን ያስባል?

የእኔ ፍላጎት ጠ/ሚኒስትሩንም ሆነ ደጋፊወቻቸውን ጥርጣሬ ውስጥ መከተት አይደለም። የእኔ ፍላጎት ፖለቲከኞቻችንም ሆኑ መላው ሕዝባችን እየተሄደበት ያለውን ነገር በአንክሮ እንዲመረምሩ መጠቆም ነው።

በመደመር ስም እየሆነ ያለውን ሁሉ እስቲ ዝም ብላችሁ አስቡት! ለችግሮችና ላለመግባባቶች መፍትሄ ለመስጠት በሚል በተለያዩ አሸማጋዮች ብዙ ጊዜ እየተሞከሩ የከሸፉ የእርቅና የድርድር ጥረቶች በሙሉ መልክ እየያዙ የመጡት ዶ/ር ዐቢይ ስልጣን ከያዙ በኋላ ነው። ግን ለምን? የተለየ ስብዕና ስላላቸው፣ መለኮታዊ ጸጋ ስለተጎናጸፉ፣ የሚፈሩበት ወይም የሚከበሩበት ስውር ኃይል ከጀርባቸው ስላለ፣ ወይስ ምን?

ዶ/ር ዐቢያ ወደስልጣን ከመምጣታቸው በፊት በአንዳንድ የየክልሉ አመራሮች የሚደገፉ የሕዝብ ተቃውሞወች እዚህም እዚያም እየተቀጣጠሉ ነበር። ተቃውሞውን ተከትሎ በኢሕአዴግም በሕወሀትም ውስጥ መከፋፈል እንደተፈጠረ ይወራ ጀመር። በመጨረሻ ከዚያው ከኢሕአዲግ ውስጥ የለውጥ ኃይል አሸንፎ ስልጣኑን ተቆጣጠረ ተባለና ብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ ፌስታ አደረገ። የለውጥ ኃይል የተሰኙት የገዱ ቡድን አባላት ለጠ/ሚኒስትርነት በእጩነት ያቀረቡትን አቶ ደመቀ መኮንንን ራሱን ከውድድር እንዲያገል አድርገው ድጋፋቸውን ለዶ/ር ዐቢይ ሰጡ። ዶ/ር ዐቢይ ስልጣኑን እንደተረከቡ "ከእንግዲህ በኋላ አንዱ ሌላውን በጉልበት አሸንፎ ወደስልጣን የሚወጣበት፣ ተሸናፊ ተሳዳጅ የሚሆንበት ታሪክ ማብቃት አለበት! የፖለቲካ ፓርቲወች ተቃዋሚወች ሳይሆኑ ተፎካካሪወች ነው መባል ያለባቸው። የሚሾመውም የሚሽረውም ሕዝብ ነው፤ በዚህ እስካመንን ድረስ አጀንዳችንን ለሕዝብ አቅርበን ውጤቱን በጸጋ እንቀበል ብለው" በሀገራቸው ላይ ሆነው በሰላም እንዲታገሉ ለሁሉም የተቃዋሚ ድርጅቶች ጥሪ አደረጉ። በአሸባሪነት ተፈርጀው የነበሩት ግንቦት 7፣ ኦነግና ኦብነግ ስማቸው ከአሸባሪወች መዝገብ ተፍቆ የተከፈተባቸው የክስ ፋይል ተዘጋ።

ጥሪውን ተከትሎ የሰላም ታጋይ ሆኘ ስታጋል ነበር፣ በትጥቅ ትግል ተፋላሚ ነበርሁ፣ የሲቪክ ድርጅት መስርቸ ስለዴሞክራሲና የሕዝብ መብት ተከራክሪያለሁ፣ የሀገር ቤትን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ስመራ የቆየሁ አክቲቪስት ነኝ ባዩ ሁሉ ወደሀገር ቤት ተመመ።

ዶ/ር ዐቢይ በዚህ አላበቁም። ወደኤርትራም ጎራ ብለው ከአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ተቃቅፈው እርቅ አወረዱ። አቶ ኢሳያስም በተራቸው ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ ተጋብዘው ሲመጡ ደማቅ አቀባበል ተደረገላቸው። እሳቸውም አክብሮ የተቀበላቸውን ሕዝብ አክብረው በረሱት አማረኛ ቋንቋ ንግግር አደረጉ። በሆነው ሁሉ የተደመሙ ሰዎች ዶ/ር ዐቢይ ኢትዮጵን ለመታደግ ከፈጣሪ የተላኩ ዳግማዊ ሙሴ ናቸው እስከማለት ደረሱ።

ይህ ሁሉ የሆነው ግን ኤች አር 128 የተሰኘው ሕግ በአሜሪካው የሕግ መወሰኛው ም/ቤት የመጽደቁ ነገር እርግጥ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በቀጠለ ሂደት ነው። በዚህ የጊዜ ሂደት ውስጥ የሕወሀት ሰዎች ከማጉረምረም አልፈው በራሳቸው ያደረጉት አንድም የተቃውሞ እንቅስቃሴ አልነበረም ማለት ይቻላል።

ችግሮች ግን ከመቀነስ ይልቅ ይበልጥ እየተደራረቡ ፋታ የሚነሱ መሆናቸው አልቀረም። ዶ/ር ዐቢይ ስልጣን ይዘው ገና ትንፋሻቸውን ሳይሰበስቡ እርሳቸውን ለመደገፍ መስቀል አደባባይ በተጠራው ሰልፍ ላይ የተደራጀ የተባለ የቦምብ ጥቃት ደረሰ። ጥቃቱን በተመለከተ ምርመራ ለማድረግ የአሜሪካው FBI ይሳተፋል ተብሎ የነበረ ቢሆንም በኋላ ግን በምርመራ ሂደቱ ውስጥ እንዳልተሳተፈ ተገልጿል። ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከፌደራል መረጃና ደኅንነት ኮሚሽን እና ከፌደራል ጠ/አቃቢ ሕግ የተውጣጡ ባለሙያወች የተሳተፉበት የምርመራ ቡድን ይፋ እንዳደረገው የቦንብ ፍንዳታው የተፈጸመው "ኢትዮጵያ መመራት ያለባት በኦነግ ነው" በሚሉ ሰዎች በተደራጀ ኃይል እንደሆነ ነው። ይህን የጥፋት ኃይል የመራችው ኬንያ የምትኖር ገነት ታምሩ (ቶለሺ ታምሩ ) የምትባል የኦነግ አባል እንደሆነችና የጥቃቱ አላማም ጠ/ሚኒስትሩን መግደል እንደነበር ተገልጿል። በሰላም ገብቶ በሰላም እንዲታገል ጥሪ የተደረገለት ኦነግ በሽብር ሥራ መሰማራቱን ባለመተው ጠ/ሚኒስትሩ ርምጃ ይወስዳሉ ብለን ስንጠብቅ እርሳቸው ግን "በሽብር ተግባር ከለውጥ ጉዞ አንገታም" የሚል ንግግር አሰምተው በሳቸው አባባል ትዕግስት ማድረግን መረጡ። ብዙም ሳይቆይ የታጠቁ የኦነግ ወታደሮች እዚህም እዚያም ችግር መፍጠሩን ተያያዙት፤ "እረፉ!" ያላቸው ግን አልነበረም። አሶሳ ላይ የከማሼ ዞን አመራሮችን በመግደላቸው ለበርካታ ሰዎች መሞት፣ ለንብረት መውደም እና ከአንድ መቶ ሃምሣ ሺህ በላይ ለሆነ ሕዝብ መፈናቀል ምክንያት ሆኑ። በባሌ፣ በምሥራቅ ሀረርጌ፣ በድሬዳዋ፣ የብዙወችን ሕይወት እንደቀልድ ቀጠፉ። ሻሸመኔ ላይ ዘቅዝቀው ሰቅለው አንድ ንጹህ ወንድማችንን በጭካኔ ለህልፈት ዳረጉ። ቡራዩ ላይ "መጤ!" ያሏቸውን ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ገደሉ፣ ንብረት አወደሙ፤ ቁጥሩ ከአሥራሦስት ሺህ በላይ የሚገመት ሕዝብ አፈናቀሉ። ወለጋ ውስጥ የተወሰኑ አካባቢወችን በነጻ መሬትነት ይዘው አስተዳደር መስርተዋል፤ ሰራዊት መልምለው እያሰለጠኑ ነው፤ በተለይ አማራ ናቸው የተባሉትን ሰዎች እየመረጡ ትጥቅ አስፈትተዋል፣ ከመንግሥት ካዝና መሳሪያ እየዘረፉ የራሳቸውን ሰው እያስታጠቁ ነው። ኦነግ ትጥቅ እንዲፈታ መንግሥት ያቀረበውን ጥያቄ የድርጅቱ መሪ አቶ ድውድ ኢብሳ "ትጥቅ አስፈችም፣ ትጥቅ ፈቺም አይኖርም" ብለው ጥያቄውን አጣጥለውታል። ይህን አስመልክተው ዶ/ር ዐቢይ ያሉት ነገር ቢኖር "የአፍ ወለምታ ሊሆን ይችላል፤ ለማንኛውም እናነጋግራቸዋለን" ነው። ይህ ሁሉ የሚሆነው አቶ ዳውድ ኢብሳ ከሀገር ሰላም እና ከዜጎች ህልውና ይበልጥ ተከብረው አዲስ አበባ ተቀምጠው ነው። በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ከተማ ም/ከንቲባ ታከለ ዑማ በከተማው ወጣት ስም ከአዲስ አበባ ውጪ የመጡ ኦሮሞወችን ሰብስበው እንዳወያዩ ሰምተናል። ጥቂት ቆይቶ ከሌላ አካባቢ ተደራጅተው የመጡ ናቸው የተባሉ ኦሮሞወች በአዲስ አበባ ውስጥ ያሉ ባዶ ቦታወችን እየተቀራመቱ እንደሆነ እየተወራ ነው። የአዲስ አበባ መገናኛ ብዙሀን ኤጀንሲ ሃላፊወች ሆነው የተሾሙት በሙሉ ኦሮሞወች ናቸው ተብሎም ሰምተናል።

ከሰሞኑ ደግሞ የታጠቁ ወታደሮች ቤተመንግሥት ድረስ ዘልቀው የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ እንዳደረጉ በመንግሥት ቴሌቪዥን ሳይቀር ተነግሮናል። የሚገርመው ግን ጠ/ሚኒስትሩን ሊገድሉ የሄዱት ታጣቂወች ትጥቅ ፍቱና ግቡ ሲባሉ እሺ ብለው ትጥቅ ፈትተው ቤተመንግሥት ቅጽር ግቢ መግባታቸው እና "የደመወዝና የጥቅማጥቅም ችግር አለብን" የሚል ቅሬታ አንስተው በዚሁ ጉዳይ ላይ ከጠ/ሚኒስትሩ ጋር ውይይቱን በሰላም ጀምረው በሰላም ማጠናቀቃቸው ነው። ከቀናት በኋላ ዶ/ር ዐቢይ በፓርላማ ላይ በሰጡት መግለጫ ለጥፋት የመጣውን ኃይል በብልሀት እንዲመለስ በማድረጋቸው "ሳንገድለው አመለጠን!" ብለው የተቆጩ ሰዎች እንዳሉ ተናግረዋል። "ወይ እንጨፍልቅ፣ እንደፍጥጥ፣ እንሰር እና ጸረ-ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እንሁን፤ አይ ችለን ዋጋ ከፍለን እንሻገር ከተባለ ፈተናው ከባድ ነው፤ ትልቁ ፈተና የማይነገር፣ የማይዘረዘር ከውስጥ የሚነሳ ነው" ብለዋል ጠ/ሚኒስትሩ። በህይወት እየተወራረዱ ለውጡን ለማስቀጠል ጥረት እያደረጉ ያሉትን የለውጥ ኃይሎች ሕዝብ ሊደግፋቸው ካልቻለ በዚህ ሁኔታ መቀጠል እንደሚቸገሩ ነው ያስገነዘቡት።

ጠ/ሚኒስትሩ ባይኖሩ ከዚህ የበለጠ ምን አይነት ችግር ሊፈጠር ይችል እንደነበር አላውቅም፤ በእርሳቸው ጊዜስ ቢሆን ምን ያልሆነ ነገር አለ! የከፋው ችግር ውስጣዊ ነው በሚሉት ላይ ዕውነትነቱ አጠያያቂ አይመስለኝም። ከውጪ ሆኖ ያውክ የነበረው ቅጥረኛ ሁሉ ተደምሪያለሁ ብሎ ወደሀገር እንዲገባ ከተደረገ ታዲያ ከውጭ የሚነሳ አዋኪ ከየት ይመጣል። የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚባሉት ሀገሮች ሲዋጉን የነበሩት በቅጥረኞች እንጂ ራሳቸው ጦር አዝምተው አልነበረም። ችግሩ ውስጣዊ ነው ሲሉ ችግር ፈጣሪወች በድርጅታቸው ውስጥ ያሉ ሰዎች መሆናቸውን መግለጻቸው ይሆን!

ችግሩ ለሕዝብ የማይነገር የሆነበት ምክንያትስ ምን ይሆን? የኦነግ ዕብሪት፣ የመንግሥት ዝምታ፣ የወያኔ ድምጽ ማጥፋት፣ የፕሬዚደንት ኢሳያስ ቤተኝነት፣ የአዲስ አበባ ወጣቶች አፈሳ - - - ሚስጥር፣ በጥልቅ ቢፈተሽ መልካም ነው። እንደ እኔ ግምት ከሆነ ከሁሉም ነገሮች ጀርባ ወያኔ አለ። ወያኔወች በህሳብ ልዩነት ተጨቃጭቀው ሊሆን ይችላል እንጂ ወደከረረ ጠብ ገብተው መከፋፈል ደረጃ አልደረሱም። ሁሉም በአንድነት አብረው እየመከሩ እየዘከሩ ተስማምተውና ተደጋግፈው እየኖሩ ነው ያሉት። አንድም ወታደር አልቆሰለባቸውም፤ አልተማረከባቸውም፤ አልሞተባቸውም። ዋናው የሀገሪቱ ወታደራዊ ኃይል ያለው ትግራይ ነው። ተዋጊ አውሮፕላኖች እና ሄሊኮፕተሮችም እዚያው ነው ያሉት። የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹመቱ በእጃቸው ነው። ዜናው ሁሉ ስለኦነግ በመሆኑ በሰው አፍ ገብተው መብጠልጠሉ ቀርቶላቸዋል። ከበፊት ጀምሮ ስጽፍ የነበረው የኦነግ እና የወያኔ ቅራኔ "የስጋ ትል፣ የዘመድ ጥል" የሚሉት አይነት እንደሆነ ነው። ኢሕአዴግም ውስጥ ወያኔ አለ። ዶ/ር ዐቢይ ኦሮሚያን እያጠናከሩ፣ ለወያኔ ሰዎች ሽፋን እየሰጡ፣ ለትግራይ ትግርኝ መብቀያ መሬት እያቀለዙ ይሆን!

የሆነው ሆኖ በሰላም መድረስ ከቻልን በሚቀጥለው ምርጫ የተወሰነ ወንበር ለተቃዋሚዎች ለመልቀቅ እንደተፈለገ በግልጽ የሚታይ ነገር አለ። ወያኔ እንደጉድ የሚፈራውን የአሜሪካን ግልምጫ ለማለዘብ ከዚህ የተሻለ አማራጭ አይኖረውም። እና 100 የፓርላማ መቀመጫ ለየተቃዋሚው በኮታ ቢያከፋፍል ከውጪም ከውስጥም ሙገሳ እንደሚዘንብለት አያጠራጥርም። ከአምስት አመት በኋላ አንድ ተጨማሪ ወንበር ከለቀቀ 'አይ ጥሩ ነው፣ ለውጥ አለ!" የሚሉ አይጠፉም። ገዢ ፓርቲ ሆኖ መንግስት ለመመስረት 275 የፓርላማ መቀመጫ ማሸነፍ ቢያስፈልግ በየአምስት አመቱ ምርጫ በሚገኘው አንድ ተጨማሪ ወንበር "ጥሩ ነው፣ መሻሻል አለ" እየተባለ ኢሕአዴግ ስንት አመት ሊገዛን እንደሚችል ማስላት ይቻላል። በምርጫ መሸናነፍ ይኖራል ብየ ተስፋ የማደርግ ብሆን ልመክረው የምችለው "ምርጫ ውስጥ ከመግባታችን በፊት በሽግግር ጊዜ ሊሰሩ የሚገባቸውን ነገሮች የሚሰራ ከኢሕአዴግ ቁጥጥር ነጻ የሆነ የሽግግር መንግሥት እንዲመሰረት መታገል ብቸኛው አማራጭ መንገድ ይሆናል፤ የውድድር ሜዳውን ሳያስተካክሉ ወደጨዋታው ከገቡ በኋላ የተሸነፍነው ስለተጭበረበርን ነው ብሎ መጮሁ ዋጋ አይኖረውም" ብየ ነው።

በኢሕአዴግ አባልነታቸው የሚታወቁት አራቱ ድርጅቶች ባልወከላቸው ሕዝብ ላይ ነግሰው ለመከራ ከዳረጉን እንደቀልድ 27 አመታት አለፉ። በእነዚህ አመታት ውስጥ ስንት ግፍ ተሰራ! በቅኝ ግዛት ይገባኛል ጥያቄ ጠብ ውስጥ ላለመግባት ሲሉ እ.ኤ.አ በ1884 የአፍሪካ ሀገሮችን ለመከፋፈል በርሊን ላይ እንደተስማሙት ኃያላን ሀገራት፣ የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችም የሕዝብን ፍቃድ ሳይጠይቁ በትግራይ፣ በአማራ፣ በደቡብና በኦሮሚያ ስም ተከፋፍለው ይዘው ደም እያስለቀሱ መግዛታቸውን ቀጥለዋል።

በእኛ ሀገር አረዳድ "ፖለቲካ" ማለት ወደ ሀብት ማፍሪያ እና ሀብት ማስጠበቂያ ስልጣን የሚወስድ አውራ መንገድ ማለት ነው። ተመሳሳይ ፍላጎት አለን የሚሉ ፖለቲከኞች ተደራጅተው፣ የሕዝብን ጥያቄ አንግበው፣ በዚህ መንገድ ተጉዘው ተሳክቶላቸው ስልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ለብዝበዛ እንዲመቻቸው ሕዝቡን በተለያየ መንገድ ጠርንፈው ይይዙታል። "ሰላም ለማስጠበቅ" በሚል ሽፋን ስለዴሞክራሲ የሚጮኸው ሕዝብ ላይ ጦራቸውን እያዘመቱ ችግር ፈጣሪ ናቸው የሚሏቸው ሰዎች ላይ ርምጃ በመውሰድ ተራቸው ደርሶ በሌላ በተደራጀ ኃይል እስኪወገዱ ድረስ በአምባገነንነት ይቀጥላሉ። የሀገር ችግር የሚፈታው ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሲሰፍን፤ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ስርአት የሚሰፍነው የፖለቲካ ነጋዴዎችን ማስቆም ሲቻል በመሆኑ በሚተውኑት ተውኔት ሳንታለል የፖለቲካ ነጋዴዎችን ወዲያ አሽቀንጥረን ልንጥላቸው ይገባል። ወዶም ፈርቶም ሕዝብን የሚያከብር መንግሥት እንጂ ወንበዴ እንዲገዛን መፍቀድ ተገቢ አይደለም።

**ጎጃምን አልረሳም**

በአማራ ስም ተጠርንፈው ከተያዙት ተገዥወች ውስጥ አንዱ የሆነው ጎጃም ከስልጣንም ከልማትም ተገፍቶ በግብር ከፋይነትና በወታደርነት ተግባር ብቻ እንዲወሰን ከተፈረደበት 27 ዓመታት አለፈው። ይህን ዕኩይ ሴራ ተቃውሜ በመጻፌ ገዥዎች ባሰማሯቸው ሰዎች ከፍተኛ ውግዘት እየደረሰብኝ ነው። ግን ለምን? የዶ/ር ዐቢይ የካቢኔ ሹመት አማራን ያገለለ ነው ለማለት የደፈረ ሰው እንዴት ብሎ ነው በአማራ ክልል ውስጥ ጎጃም ከስልጣንም ከልማትም ቢገለል ችግር የለውም ለማለት የሚደፍረው? ጎጃሜዎች በጎንደርና በወሎ በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር ቦታወች ላይ አይታዩም። ራሳቸውን በራሳቸውም እያስተዳደሩ አይደለም። ይህ ነው የሚባል የልማት ሥራም አልተሰራላቸውም። ታዲያ ይህን ድርጊት ተቃውመን ድምጻችንን ለማሰማት ያልቻልንበት ምክንያት ምንድን ነው? "በወሎና በጎንደር እየተገዛን ነው አትበሉ፤ ይኸ ዘረኝነት ነው" የሚሉ እፍረት የሌላቸው ሰዎች "አርፋችሁ ተገዙ!" ብለው ለመናገር ሲደፍሩ ይህን ተቃውመን በደላችንን ለማሰማት እንዴት እንፈራለን፤ እንዴት ቆርጠን ለትግል አንነሳም። አንዱ ምን እንዳለኝ ታውቃላችሁ? "ይህን የምታደርገው አቶ እንትና ነህ አይደል፤ አውቀንሀል" ብሎ የሆነ ሰው ስም ጠርቶ በፌስቡክ መልዕክት ሊያሸማቅቀኝ ሞከረ። አቶ እንትና በአካባቢ የተሰባሰቡትን ሰዎች አፍራሽ እንቅስቃሴ እየታገለ ስለጎጃሞች መብት ሲከራከር እንደነበር ከዚህ ሰውየ አነጋገር መረዳት ቻልሁ።

የጎጃም ሕዝብ ጎጃሜ ነው። በወያኔ ጊዜ ከመፈጠሩ በፊት አማራ የሚባል ጎሳ መቼም አልነበረም። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም፣ ዶ/ር ኃይሌ ላሬቦ ይህንን ሀቅ መስክረዋል። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም በአንድ ወቅት አማራ የክርስትና እምነት ተከታዮች የሚጠሩበት የጋራ ስም እንጅ የጎሳ ስም አይደለም ብለው ተናገሩ ተብሎ የደረሰባቸውን ውርጅብኝ እናስታውሳለን። ኢትዮጵያ ውስጥ ሀቅ መናገር ያዋርዳል። በሀገራችን ታሪክ ጉልህ ስም ያላቸውን እኒህን አባት አማራ የሚባል ጎሳ በታሪክ አይታወቅም ስላሉ አሁን አማራ በሚባለው ክልል የሚኖረውን ሕዝብ ህልውና እንደካዱ ተቆጥሮ ሲያበሻቅጧቸው የነበሩት በአማራ ስም ጠቅልለው እየገዙ ያሉ የአዴፓ አድራጊ ፈጣሪዎች ጀሌዎች ናቸው። አማራ የክርስትና ዕምነት የወል መጠሪያ መሆኑን ለማወቅ ቀደም ባሉት ጊዜያት የተጻፉትን መጽሀፍት ማገላበጥ በቂ ነው። ታሪክ በተለያየ መንገድ ይገለጻል። ማህበረሰቡ ይጠቀምባቸው የነበሩትም ሆኑ በትምህርት የምናውቃቸው አባባሎች የሚመሰክሩት ይህንኑ ሀቅ ነው። ለምሳሌ ሁለት ሰዎች የምር ጠብ ውስጥ ሲገቡ

"ከእንግዲህ እኔና አንተ እስላምና አማራ ነን" ነበር የሚባባሉት፤ ተቆራርጠናል ለማለት።

በትምህርት ቤት እያለን ሰምና ወርቁን እንድንለይ ከሚቀርቡልን ቅኔወች ውስጥ
ተነካክቶ ከእስላም ጋራ
እንግዲህ ምኔ አማራ
የሚል እንደነበረ ብዙወቻችን እናስታውሳለን። ከዚህ ምን እንረዳለን?

አማራ የጎሳ መጠሪያ አይደለም እንጅ ነው ቢባል እንኳ የአማራ ቋንቋ ነው የሚባለውን አማረኛ የተናገረ ሁሉ አማራ ነው የሚያሰኝ አሳማኝ ምክንያት አይኖርም፤ እንግሊዝኛ ተናጋሪው ሁሉ እንግሊዝዛዊ እንዳልሆነው፤ አረብኛ ተናጋሪው ሁሉ አረብ እንዳልሆነው፣ - - - ማለት ነው። አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ አውስትራሊያ፣ ካናዳ፣ ጃማይካ፣ አየርላንድ፣ ኒውዚላንድ፣ ግሪናዳ - - - እንግሊዝኛ ተናጋሪወች ናቸው። ግን ሁሉም የየራሳቸው ሀገርና ማንነት አላቸው። የጎጃም ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ረጅም ታሪክና ማንነት ያለው ጎጃሜ ነው።

ከኢሕአፓ ከድተው ለወያኔ ባደሩ ሰዎች የተመሰረተው ኢሕዴን፣ ደርግን ይዋጋ የነበረው ለትግራይ አዋሳኝ በሆኑት በሰሜን ወሎና በሰሜን ጎንደር አካባቢ እንደነበረ ይታወቃል። በዚህም ምክንያት አብዛኛው የኢሕዴን ታጋይ ከጎንደርና ከወሎ በተሰባሰቡ ሰዎች የተሞላ ነበር። እንግዲህ ለእነዚህ ሰዎች ነው በትግሉ ወቅት ላደረጉት ድጋፍ 'ጎጃም የደማችሁ ካሳ ነው' ተብለው እንደፈለጉ እንዲያደርጉት የተሰጣቸው። ስጦታውን ለመቀበል የራሳቸው አካል የሆኑትን ወልቃይትና ራያን በእጅ መንሻነት ለትግራይ ማስረከብ ስለነበረባቸው ካለምንም ተቃውሞ ፈጽመውታል። እኒህ ህሊና ቢሶች የራሳቸውን ሕዝብ አሳልፈው መስጠታቸው ሳያንስ የሕዝቡን መከራ ከምንም ባለመቁጠር ከወያኔ በላይ ወያኔ ሆነው "ብአዴን በወልቃይት ጉዳይ አያገባውም፤ የወልቃይት ጉዳይ የትግራይ የውስጥ ችግር ነው፤ እኛን አይመለከተንም" እያሉ ሲከራከሩ እንደነበር ማናችንም አንረሳውም። የሕዝብ አልገዛም ባይነት እየተፋፋመ ሲመጣ "ለውጥ እያደረግን ነው" የሚል ሌላ ቀልድ ፈጥረው፣ ተቃዋሚውን ሳይቀር ከትግል አዘናግተው ስልጣናቸውን አደላድለዋል። ጎጃም ግን ያው እንደባለፈው ሁሉ በተገዥነት ስም እንደቀጠለ ነው። አንዱ ጓደኛየ፣ "ዝም ብለህ ብቻህን ትጮሀለህ እንጂ ጎጃም መቼ ተበደልሁ አለ፤ ተስማምቶት በሰላም እየኖረ አይደለም እንዴ!" አለኝ። ዕውነቱን ነው የራስን በራስ ማስተዳደር መብት መነጠቅ ማለት ባርነት መሆኑን ተምረናል የሚሉት ሁሉ አምነው ሊቀበሉት የቻሉ አይመስለኝም። ሰው እንዴት ባርነትን ይመርጣል? ጠላቶቹ እንዲገዙት መብቱን አሳልፎ መስጠት ምን ማለት ነው!

አሁን የለውጥ ኃይል ነን የሚሉት የአዴፓ ሰዎች አይደሉም እንዴ የጎጃምን ሕዝብ ጠበንጃ ደብቀሀል እያሉ የገደሉት፣ የገረፉት፣ አስረው ያሰቃዩት፣ ከመሬቱ የነቀሉት። የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም የወሰዳችሁትን ብድር አልመለሳችሁም በሚል የቤት ቆርቆሮ እያስገነጠለ ስንቱን የጎጃም ሰው ቤት አልባ አላደረገም? የእርሻ በሬወችን አሸጦ ለስደት አልዳረገም? ጉራፋርዳ ምስራቅ ጎጃም ሆኗል ተብሎ ተሰዶ ከሚኖርበት ቦታስ ያፈራውን ሀብት ተነጥቆ እንዲባረር አልተደረገም? ከራሱ ምድር ከመተከል "መጤ!" ተብሎ አልተሰቃየም? ይህ ሁሉ ግፍ ሲፈጸምበት ወረዳ፣ዞን፣ ክልል ላይ ነግሰው የነበሩ ባለስልጣናት እነማን ነበሩ? አሁንስ የለውጥ ኃይል ነኝ እያለ የሚቀልደው ማነው? ይህ የለውጥ ኃይል ነኝ ባዩ ከየት የመጣ ነው? በፊት በስልጣን ላይ ከነበሩት ሰዎች ውስጥ በሰሩት ሥራ የተቀጣ ማን አለ? እየሆነ ያለው በፊት የተፈጸሙት ግፎች ሁሉ በወያኔ ተሳበው የለውጥ ኃይል የሚባለው ቡድን ከወንጀል ነጻ የሆኑ አርበኞች ስብስብ እንደሆነ አስመስሎ መስበክ ነው። ተልዕኮ ተሰጥቷቸው በውጭ ሀገር ሳይቀር ተሰማርተው በብዙሀን መገናኛ ይህንን የሚያስተጋቡ በሙሉ፣ ገዥወቻችን ከበቀሉበት አካባቢ የተገኙ የኮር አባላት ናቸው።

እኛ ገዳይ አስገዳዮቻችንን አውቀናል። እንዳንናገር አፍኖ፣ እንዳንፈራገጥ እግር ከወርች አስሮ መከራችንን ሲያበላን የኖረው ከወሎና ከጎንደር በተውጣጡ ጋንግስተሮች የተመሰረተው የበፊቱ ብአዴን የአሁኑ አዴፓ ነው። ለእኛ ለጎጃሞች ቁጥር አንድ ጠላታችን አዴፓ ነው። ጎጃም ውስጥ አፈናና ግድያ ይፈጽም የነበረው ወያኔ አልነበረም፤ ሕዝብን ሲያስር፣ ሲገርፍ፣ ሀብት ሲዘርፍ፣ ከመሬትና ከሥራ ሲነቅል የነበረ ወያኔ አልነበረም፤ አዴፓ ነው። በወያኔ ቀጥተኛ ተሳትፎ የተፈጸመ ወንጀል ካለም የወንጀሉ ዋና ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው አዴፓ ነው። ሕዝቡን ከጥቃት መከላከል ካልቻለ ለምን በስልጣን ላይ ቀጠለ?

ከዚህ በፊት በጻፍኋቸው ጽሁፎች የወሎንም ሆነ የጎጃምን የበላይነት ለማስፈን የተደረገ እንቅስቃሴ አልነበረም ማለቴ ይታወሳል። በነዚህ አካባቢወች የተደረጉ እንቅስቃሴወች ራስና በራስ የማስተዳደርን መብት ለማረጋገጥና ግዛትን ለማስጠበቅ የተደረጉ እንቅስቃሴዎች እንደሆኑ ገልጬ ነበር። መሳሳቴን ያወቅሁት በአማራ ስም የወሎና የጎንደርን የበላይነት ለማስፈን እና የበላይነትን አስጠብቆ ለማስቀጠል እየተሄደ ያለበትን መንገድ የሚያሳይ መረጃ ከደረሰኝ በኋላ ነው። በእርግጥ ቀደም ብየ የማውቃቸው አንዳንድ ነገሮች ቢኖሩም ያን ያህል ትኩረት አልሰጠኋቸውም ነበር። አስብ የነበረው ሁላችንም የወያኔ ተጠቂወች እንደሆን ነበር። "የሰው የለው ሞኝ" ነው ያለው ዘፋኙ! ለካስ በአማራ ክልል ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ያለው የጎንደርና የወሎ ጥምር የገዥ መደብ፣ የጎጃምን ሀብት እየዘረፈ ሕዝቡን ተገገር አድርጎት ኖሯል። መረጃውን ካገኘሁ በኋላ ነገር እያነፈነፍሁ በጎጃም ላይ የሚሰራውን ደባ የበለጠ ለማወቅ ቻልሁ። ዛሬ ያነበብሁት ጽሁፍ ደግሞ አግራሞት ጭሮብኛል። የሰሞኑ የሚኒስትሮች ሹመት አማራውን ያገለለ ነው በሚል የአዴፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ደስተኛ አለመሆናቸውን ገለጹ ይላል። አይገርምም! አማራነት መጠርነፊያ መሳሪያ መሆኑን ሳላውቅ "አማራ በአማራነቱ ተደራጅቶ ራሱን መከላከል አለበት" እያልሁ ያዙኝ ልቀቁኝ ስል የቆየሁባቸው ጊዜያት በባከኑ ጊዜያትነት ይመዝገቡልኝ። "ሁላችንም አማራ ነን" እያሉ በአፍ እየደለሉ እንደጎጃም ተገፊና ተገገር አድርገው እየተጫወቱብን ያሉት ሰዎች በቃችሁ ሊባሉ ይገባል።

የጎጃም ህልም አቶ ደመቀን ም/ጠ/ሚኒስትር፣ አቶ ገዱን የአማራ ክልል ፕሬዚደንት፣ - - - ሆነው ማየት አይደለም። የጎጃም ሕዝብ ፍላጎት ራሱን በራሱ እያስተዳደረ በሀገር ደረጃ ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖረው ማድረግ ነው። "አቶ ደመቀ ም/ጠ/ ሚኒስትር ሆኗል፤ አቶ ገዱ የአብክመ ፕሬዚደንት ሆኗል፤ ጄኔራል ማንቴስ የአማራ ክልል ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ ሆኖ ተሹሟል፤ ይህ ሁሉ የሆነው በትግላችን ነው። የአዲስ አበባ ከንቲባ ቦታ፣ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ቦታ፣ - - - ከእጃችን እንዳይወጣ መታገል አለብን" እያሉ ሲቀሰቅሱን የነበረው በእኛ ትወከላላችሁ ለማለትም አይደል! ከእነዚህ ሁሉ የእኛ ሰው እስቲ የቱ ነው?

የምደግፈው መልካም የሆነውን ሁሉ ሲሆን የምቃወመው ደግሞ መጥፎውን ነው። መልካም አድራጊ ሰው ካለ ማንም ይሁን ማን እደግፈዋለሁ። መጥፎ የሚሰራው ሰው የቅርብ ወገኔ ቢሆን እንኳ ዕውነት ዕውነት እላችኋለሁ ደግፌው አልቆምም። ወያኔን ስቃወም የነበርሁት በመጥፎ ድርጊቱ እንጂ የትግራይ ድርጅት ስለሆነ አልነበረም። እንደእኔ እምነት የማያግባባን መጥፎ ድርጊት እንጂ መልካም ተግባር አይደለም። ፕሮፌሰር መስፍንን ከምወድበት ምክንያት አንዱ የሚናገሩትም ሆነ የሚያደርጉት ማንንም ለማስደሰት ወይም ለማስቀየም ሳይሆን ዕውነትን ለመመስከር በመሆኑ ነው። እኒህ ምሁር በኃይለስላሴም፣ በደርግም፣ አሁንም በኢሕአዴግ ጊዜ፣ እንከኖችን እየነቀሱ በማውጣት በድፍረት ሲሞግቱ የኖሩ ሰው ናቸው። "እንዲያው ምኑ ነው የሚጥምህ?" ተብለው የተጠየቁ እሳቸው መሰሉኝ፤ ሁሉንም መንግሥታት ተቃውመው በመቆማቸው። እኒህ ሰው የሚደግፉት ግለሰብን ወይም መንግሥትን ሳይሆን መልካም ተግባርን ነበር። መንግሥታት በጎ ነገር የራቃቸው በመሆናቸው፣ በሚሰሯቸው መጥፎ ስራወች ነው ሲቃወሟቸው የኖሩት፤ አሁንም እየተቃወሙ ያሉት።

እኔም ብሆን ከዚህ የተለየ ነገር እያደረግሁ አይደለም። ክፉ ተግባርን እየነቀፍሁ በሰላም የሚያኗኑረንን እያመላከትሁ ነው። ሁላችንም በየጎጇችን ብንሰባሰብ መቸ ክፉና ደግ እንነጋገር ነበር! አሁንም ቢሆን የሚበጀን "አንችም አባ ወራ እኔም አባወራ" እየተባባልን ከመተራረብና በጥላቻ ከመተያየት ወጥተን ጥሩ ጎረቤታሞች ሆነን በመከራም በደስታም ጊዜ መረዳዳት ነው።

በመጨረሻም ለማሳሰብ የምፈልገው ስለሸዋ የገዥ መደብ ሳነሳ የሸዋን ህዝብ እንደምጠላ አድርገው የሚናገሩ፣ ወያኔን ተቃውሜ ስጽፍ የትግራይን ህዝብ እንደማልወድ አድርገው የሚያስቡ፣ በአዴፓ ውስጥ ተሰባስበው በህዝብ ላይ የሚቀልዱትን ሳጋልጥ በወሎና በጎንደር ላይ እንደዘምትሁ አድርገው የስድብ ናዳ የሚያወርዱትን አደብ እንዲገዙ ነው። እኔ ከገዥ መደቦች እንጂ ከህዝብ ጋር ጠብ ሊኖረኝ አይችልም። የትኛውም ህዝብ ለእኔ ወገኔ ነው። ለዚያም ነው ለወልቃይትና ለራያ ስጮህ የኖርኩት።

ግራም ነፈሰ ቀኝ ጎጃም የራሱ ጌታ ለመሆን ከአማራነት የአፈና ከረጢት አፈትልኮ መውጣት አለበት። መተዳደርም ሆነ መወከል ያለብን በራሳችን ሰዎች ብቻ ነው ብለን ለመከራከር፣ ሰሚ ካጣን ደግሞ ለመታገል መቁረጥ ይኖርብናል። አዎ! ጎጃም በጎጃሜነቱ ተደራጅቶ ጠላቶቹን አምርሮ ሊታገል ይገባል። ራሱ መርጦ በሚሾማቸው ሰዎች ካልሆነ በስተቀር አማረኛ ተናጋሪውም ሆነ ሌላው ከየትም እየተጠራራ መጥቶ እንዲገዛው መፍቀድ የለበትም። በአላማ ያልተደራጀ፣ ያልሰለጠነ፣ ያልታጠቀ እና ጥሩ አመራር የሌለው ሕዝብ ምን ያህል ብዙ ቢሆን በጥቂት የተደራጁ ኃይሎች ተገዥ መሆኑ ግልጽ ነው። በገበያ መሀል አንድ የታጠቀ ሰው ተኩስ ቢከፍት ሁሉም እግሩ ወደመራው ሮጦ ለማምለጥ ይጥራል እንጂ ተኳሹን በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚሞክር ይኖራል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። ያልተደራጀ ሕዝብ ማለት እንደዚህ ነው።

ገዥወቻችን እጃቸውንም እግራቸውንም ከጎጃም ላይ እንዲያነሱ እጠይቃለሁ። የሀገርን ዕድገት ዕውን ለማድረግም ሆነ የሕዝብን ሰላምና አንድነት ለማረጋገጥ አንዳችን በሌላችን ላይ ያለንን ጥላቻና

አለመተማመን ማስወገድ ያስፈልጋል። ጥላቻና አለመተማመንን ለማስወገድ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን ማስፈን ግድ ነው። ያንን ማድረግ ካልቻልን በክፍተቱ ገብተው ሰላማችንን ለማደፍረስ ለሚፈልጉ የውጪ ኃይሎች ጥቃት እንጋለጣለን። አኮረፍሁ ያለን ሕዝብ ረግጦ በመያዝ የተወሰነ ርቀት መሄድ ይቻል ይሆናል፤ መጨረሻው ግን አያምርም።

አቶ በረከት ደ/ማርቆስ ታይቷል የሚል መረጃ ለወጣቶች እንዲደርስ በማድረግ ላቡን አንጠፍጥፎ ሰርቶ የገነባውን የወገናችንን ሆቴል በራሱ ሰዎች ጉዳት እንዲደርስበት መደረጉ በጣም አሳዝኖኛል። በረከትን ለመያዝ ከተፈለገ እና በረከት ማርቆስ ላይ ከታየ የፖሊስ ኃይሉን ልኮ በቁጥጥር ስር እንደማዋል ለምን ወጣቶችን ማነሳሳት አስፈለገ? ከጀርባ ያለው ድብቅ አላማ ምን ነበር? ለማንኛውም በፖለቲከኞች ቅስቀሳ ተነሳስታችሁ በራሳችሁ ወገንና ንብረት ላይ ምንም አይነት ርምጃ እንዳትወስዱ ለማሳሰብ እፈልጋለሁ። እንደዜጋ ለመከበር እንደጎኝሜ መቆም ይኖርብናል። የጎኝም ምሁራን እና ፖለቲከኞች ትኩረታችሁን ወደሕዝባችሁ እንድታደርጉ ጥሪየን አቀርባለሁ።

ራስን በራስ ማስተዳደር አለመቻል ከባርነት አይለይም!

የጎኝም ክልል ይመስረት!